## ለኢትዮጵያ ነጻነት የቆመው ወጣት ለማንኛውም ጋሬጣ አይበገርም

## ከቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ

### <u>የተሰጠ መግለጫ</u>

በህዳር 19 2000 ዓ.ም. (November 27 2007) Kinijit.org ተብሎ በሚጠራው ድረ-ገጽ "በወጣቱ ስም ዳግም መነገድ አይቻልም" በሚል የአማርኛና "Stop Using the Youth to Promote Hidden Agenda" በሚል የእንግልዝኛ ርዕስ ጽሁፍ ተስተናግዷል። ይህ ጽሁፍ "ከአዲስ አበባ ወጣቶች" በሚል ከመቅረቡ በቀር የአቋም መግለጫ ይሁን የግለሰብ አስተያየት የተባለ ነገር የለም። የጽሁፉ አቅራቢዎችም የድርጅት ዉክልና ይኑራቸው ወይንም በየትኛውም የቅንጅት መዋቅር ስለመታቀፋቸው የተባለ ነገር የለም። በተጨማሪም የጽሁፉ አቅራቢዎች በቁጥር ሁለት ይሁኑ አምስት የሚታወቅም ነገር የለም።

በድረ-ገጹ የተስተናገደው ይህ ጽሁፍ የኢትዮጵያ ወጣት ማህበረሰብ በምርጫ 97 ወቅት ለቅንጅት የሰጠውን ከፍተኛ ድጋፍና ከዚያም በመቀጠል የከፈለውን ከባድ መስዋእትነት ማውሳቱ የሚያስመሰግነው ሲሆን ወጣቱ ለብሩህ ተስፋና ለጠራ ዓላማ ያለውን ጉጉት ያስታወሰ ነው። በዚህም የጽሁፉ አቅራቢዎች ሊመሰገኑ ይገባል። ሆኖም ከዚያ በመቀጠል የቀረቡት የጽሁፉ አንቀጾች በአመዛኙ ስሜታዊ አልፎ አልፎም ግብታዊ በሆነና የጽሁፉን ዋነኛ ጭብጥ ለመጨበጥ በሚያስቸግር መልኩ የቀረቡ ጅምላ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው። ከጽሁፉ ማጠቃለያ ጥቂት ቀደም ብለው ከተቀመጡ አንቀጾች መካከል አንዱ የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግና በስሩ የታቀፉ ሌሎች አባል ሊጎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከት ነው።

ይህ የጽሁፉ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል።

> *"ውጪ ካሉ ደጋፊዎች የመከፋፈሉና የተለጣፊ ድርጅቶች የማቋቋሙ ተግባር የእነ አንዳርጋቸው ጽጌን የጥፋት ፈለግ የተከተሉ በወጣት ስም የወጣት ሊግ እያሉ በአንዳንድ ቦታዎች መመስረታቸው ሲገርመንና ሰለጥነዋል በተባሉባቸው አገሮች ወጣቱን ሲያሞኙት እየገረመን እያለ በአንዳንድ አፈንጋጮች አማካኝነት በአገር ቤትም መጀመራቸው የእኛን አላማና ማንነታችንን አለመረዳታቸው እንጂ በወጣቱ ስም ነግደው ምናልባት ጥቂት የአፈንጋጭ ቤተሰቦች ይከተሏቸው እንደሆን እንጂ <u>የኢትዮጵያ ወጣት በተከበሩ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል ከሚመራው ቅንጅት ፍላጎትና ውሳኔ ውጪ የሚከተላቸው አያገኙም</u>።" (መስመር በጽሁፍ አቅራቢዎቹ)*

በመሰረቱ ከቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግና በስሩ ከታቀፉ አባል ሊጎች በቀር በቅርብ የተቋቋመና መቋቋሙንም ለህዝብ ይፋ ያደረገ የቅንጅት የወጣቶች ሊግ የለም። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰው በድረ-ገጹ ላይ የተስተናገደው ጽሁፍ አንቀጽ በዚሁ የወጣት ሊግ ላይ የተነጣጠረ ስለመሆኑ ዋቢ መጥራት አያስፈልግም። ስለሆነም ምንም እንኳን የወጣት ሊጉ በዚህ መሰል እንኪያ ስላንቲያ ውስጥ መግባት ፍላጎቱ ባይሆንም ጽሁፉ ላዘለው የተሳሳተ አመለካከት ምላሽ መስጠትና ለጽሁፉ አቅራቢዎችም ስለ ሊጉ የተሻለ ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደሚገባ በመገንዘብ ይህንን መግለጫ አውጥቷል።

የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የወጣቶች ሊግ በJuly 2007 በዳላስ ቴክሳስ ከተለያዩ ስቴቶች ተወክለዉ በመጡ ወጣቶች የተመሠረተ ነው። ዓላማውም በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በቅንጅት ጥላ ስር በመሰባሰብ በሀገራችን የዲሞክራሲና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ስርዓት ለመመስረት በሚደረገው ሰላማዊ ትግል ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው። የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የወጣቶች ሊግና ሌሎች በስሩ የታቀፉ የወጣት ሊጎች ወጣቶችን በማደራጀት በማስተባበርና በመቀስቀስ ከፍተኛ ተግባር የሚያከናውኑ ወጣቶችን የያዙ ናቸው።እነዚህ ወጣቶች እንደ ማንኛውም በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ሀገር ወዳድና ወገን አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በኢትዮጵያ የሚደረገውን የሙብት ረገጣ ከፍርድ ውጪ እስርና ግድያ የክረምት ቁርና የበጋ ሀሩር ሳይበግራቸው በአደባባይና በተገኘው አጋጣሚ

ሁሉ ተቃውሞና አቤቱታቸውን ሲያሰሙ አቤት ባይ ላጣው ወገናቸው አንደበት ሁነው አቤት ሲሉ ረዥም ጊዜ አስቆጥረዋል። መሪዎቻችን በእስር በቆዩበትም ወቅት ለእነርሱ መፈታት እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደዋል።

በተለያዩ ስቴቶች የተመሰረቱት የወጣት ሊጎችም ሆኑ የሁሉም አስተባባሪ የሆነው ይህ የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የወጣቶች ሊግ ጽሁፉ እንደሚያትተው የማንኛውም ድርጅት ተለጣፊዎች ሳይሆኑ በህግና ደንብ የሚመሩ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማህበራት ብሎም የቅንጅት አካላት ናቸው። የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማህበራትም በቅንጅትና በፓርቲው ከፍተኛ አመራር አካላት ይፋዊ እውቅና የተሰጣቸውና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተዋቀሩ ሲሆን የወጣት ማህበራቱም የነዚህ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት አካል ናቸው። ስለሆነም የጽሁፉ አቅራቢዎች የድጋፍ ማህበራቱን አደረጃጀት፤ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ወጣቶች የከፈሉትን መስዋእትነትና ወደፊትም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ለመቆም ያላቸውን ቁርጠኝነት በመጠኑም ቢሆን ከግንዛቤ ቢያስገቡ ለወደፊቱ ከዚህ መሰል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዳይደርሱ ይረዳቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የጽሁፉ አቅራቢዎች ወጣቶች ተሰባስበው የወጣት ሊግ መመስረታቸው እንዳስገረማቸው ገልጸዋል። በመሰረቱ የወጣቶች መሰባሰብና የወጣት ሊግ መመስረት ምንም አስገራሚነት የለውም። በአለማችን የረዥም ጊዜ ታሪክ በተለያየ ወቅት የተለያየ ቅርጽና ይዘት ያላቸው ፖለቲካዊም ሆነ ከፖለቲካ ውጪ የሆነ ዓላማ ያነገቡ የወጣት ማህበራት በሀገራችንም ሆነ በተቀረው የዓለማችን ክፍል ተመስርተዋል። ይህ ሒደት በምንም መልኩ ያልተለመደና እንግዳ የሆነ ክስተት ባለመሆኑ የጽሁፉ አቅራቢዎች እንደ አንድ ተዓምር ቆጥረው መገረምን ሊፈጥርባቸው የሚገባ መሆን የለበትም። ባይሆን የጽሁፉ አቅራቢዎች የቅንጅት የወጣት ሊጎች ምስረታ ደስታ እንዳሳደረባቸው ቢገልጹ የተገባ ይሆን ነበር።

ጽሁፉ በመቀጠልም ሰልጥነዋል በተባሉ ሀገሮች ወጣቱ እየተሞኘ እንደሆነና ይህም እንዳስገረማቸው ገልጸዋል። በመሠረቱ የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግ መቀመጫ የሆነችው አሜሪካ በዓለማችን ካሉ የሠለጠኑ ሀገሮች አንዷ መሆኗ እውነታ ቢሆንም በዚህች ሀገር የሚገኘው ወጣት እየተሞኘ መሆኑን የሚያወሳው የጽሁፉ ክፍል ግን የጽሁፉ አቅራቢዎች ራሳቸው እንደገና ቢያጤኑት የተሳሳተና መሠረተ-ቢስ የሆነ ጅምላ ሀሳብ መሆኑን ለመረዳት ግዜ አይፈጅባቸውም። እውነታው በሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግ ስር የታቀፉም ሆነ በዚህ የዓለማችን ክፍል የሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በማንም የተሞኙና የሚሞኙ ሳይሆኑ ስለሀገራቸውና ስለህዝባቸው ሌት ተቀን የሚያስቡና ለወገን የሚቆረቆሩ መሆናቸው ናቸው። የጽሁፉ አቅራቢዎች ይህንን ከግምት ውስጥ ቢያስገቡ በውጭ ስለሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወጣት የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም ጽሁፉ በሀገር ቤት “አንዳንድ አፈንጋጮች” ብሎ በጠራቸው አካላት የወጣት ሊግ ምስረታ መጀመሩን ጠቁሞ ይህም የጽሁፉን አቅራቢዎች ዓላማና ማንነት ባለመረዳት መሆኑን ይገልጻል። በመሠረቱ የጽሁፉ አቅራቢዎች ራሳቸውን “የአዲስ አበባ ወጣቶች” ብለው ከመጥቀስ በቀር ስለመደራጀታቸውም ሆነ ስለ ዓላማና ማንነታቸው የሰጡት ግንዛቤ የለም። በመሆኑም በአገር ቤት የወጣት ሊግ ምስረታ ጀምረዋል የተባሉት ወገኖች በምን መልኩ የትኛውን የጽሁፉን አቅራቢዎች ዓላማና ማንነት መረዳት እንዳልቻሉ ግልጽ አይደለም። ነገር ግን በጽሁፉ አቅራቢዎች እንደተጠቆመው በሀገር ቤት የቅንጅት የወጣቶች ሊግ ምስረታ ተጀምሮ ከሆነም የጽሁፉ አቅራቢዎች ሊደሰቱበትና ሊያወድሱት የሚገባ ነው። የጽሁፉ አቅራቢዎች የሳቱት መሰረታዊ ሀቅ ቅንጅት ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የቆመ ፓርቲ መሆኑንና ከእነዚህ መብቶች መካከል የዜጎች በነጻነት የመደራጀት መብት አንዱና ዋነኛው መሆኑን ነው። ስለሆነም የጽሁፉ አቅራቢዎች ይህንን ከግምት በማስገባት በሀገር ቤት የሚገኙ ወጣቶች የቅንጅትን የብሩህ ተስፋ፤ የአንድነትና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ራዕይ በመደገፍ እንዲነሳሱ ቢያበረታቱ ለቅንጅት ቤተሰብም ሆነ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ባለውለታ ይሆናሉ። የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የወጣቶች ሊግም ከጎናቸው የሚቆም ይሆናል።

በማጠቃለያም በጽሁፉ እንደተጠቀሰው ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በምርጫ 97 ቅንጅትን በከፍተኛ ደረጃ መደገፋቸውና ከዚያም አልፈው የህይወት መስዋእትነት መክፈላቸው የማይታበይ ሀቅ ነው። ነገር ግን ጽሁፉ እልፍ አእላፍ ሊጋ ወጣቶች የተቀጠፉት ለነጻነት መሆኑን በሚያሳዝን መልኩ በማኮሰስ ወጣቱ የግለሰብ ሰብእና አምላኪ እንደሆነ አስመስሎ አቅርቧል። የጽሁፉ አቅራቢዎች

ከዚህም አልፈው ባሰመሩበት ሀሳባቸው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሚያውቀው ውጪ ሌላ ቅንጅት ያለ በማስመሰል ወጣቱ በኢንጅነር ሀይሉ ሻውል ከሚመራው ቅንጅት ፍላጎትና ውሳኔ ውጪ ሌላ እንደማይከተል ገልጸዋል። በዚህም ወጣቱ የግለሰቦች ፍላጎት ተከታይ እንደሆነ አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል። ሊጉ ለኢንጅነር ሀይሉ ሻውል ተገቢውን አክብሮት የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ አልፎ ግን ቅንጅት የሚመራውም ሆነ ወጣቱ የሚከተለው የእርሳቸውን ፍላጎት ብቻ እንደሆነ ተደርጎ የቀረበው ሀሳብ የተሳሳተና የድርጅትን መሠረታዊ ባህርይ ካለመረዳት የመነጨ እንደሆነ ያምናል። የድርጅት መሠረታዊ ጽንሰ-ሓሳብ እንደሚያመለክተው አንድ ድርጅት አንድ ዓይነት ራዕይ ያነገቡ ግለሰቦች በግልጽ የተቀመጠና በጋራ የተስማሙበትን ዓላማ ለማሳካት የሚያቋቋቁሙት፤ ለአሰራሩም ግልጽ የሆነ ደንብና ስርዓት የሚያወጡለትና እንቅስቃሴያቸውንም በአወጡት ደንብና ስርዓት መሠረት የሚያካሒዱበት ተቋም ነው። አባላቶቹም በግልጽ የተቀመጠውን የድርጅቱን ዓላማ የሚያራምዱ እንጂ የግለሰቦችን ፍላጎት የሚያስፈጽሙ አይደሉም። ይህም እውነታ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል በተሻለ የሚረዱት በመሆኑ ራሳቸውን ከቅንጅት በላይ አግዝፈው እንደማይመለከቱ እናምናለን። የጽሁፉ አቅራቢዎች የቅንጅትን ዐቢይ ዓላማዎች ያልተገነዘቡ ከሆነም “የቅንጅትን ማኒፌስቶ” እንዲመለከቱ እንጋብዛለን።

በአጠቃላይ የጽሁፉ አቅራቢዎች በሀተታቸው የዘነጉት እውነታ ቅንጅት ከህዝብ የተጎናጸፈው ከፍተኛ ድጋፍና ህዝቡም የከፈለው መስዋእትነት ቅንጅት አንግቦ ለተነሳው የዲሞክራሲና የአንድነት ዓላማ እንጂ ለግለሰቦች ሰብእና አለመሆኑን ነው። ይህ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍና ፍቅር ቀጣይነት የሚኖረው ፓርቲው በተነሳበት ጎዳና ጉዞውን ሲቀጥል ብቻ እንጂ የግለሰቦች ስም ተደጋግሞ ስለተጠራ አይደለም። ወጣቱ ከዚህ በፊትም ሆነ በአሁኑ ወሳኝ ወቅት የሚከተለው በትክክለኛው መንገድና በአርኣያነት የሚመሩትን መሪዎች እንጂ ጉዞዋቸው እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ የሆኑትን አይደለም።

ዛሬ ከቅንጅት ጉያ የተነሱ “እኔ ብቻ” የሚል አመለካከት ያላቸው ወገኖች ለራሳቸው በሰጡት የተሳሳተ ግምት ቅንጅትን ጠልፈው ለመጣል እየሰሩ ነው። እነዚህ ወገኖች የቅንጅት ከፍተኛ የድጋፍ ምንጭ የግለሰቦች ሰብእና ነው ብለው በማመን እነርሱ ዘወር ካሉ ቅንጅት እንደጉም የሚበን መስሎዋቸው በህልም አለም እየዳከሩ ይገኛሉ። እነዚህ ወገኖች በከፍተኛ ደረጃ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ድህነት ተንጸባርቆባቸዋል። መካሪ የሌለው ንጉስ እንዲሉ ይህን መሰል ቅዠት ማረቅና መቃወም የሁላችንም ሀላፊነት ነው።

ስለሆነም ሁሉም የቅንጅት ቤተሰብ የአንድነትና የፍቅር ሸማ በመላበስ ለሀገራችን ህልቁ መሳፍርት ችግር ዋነኛ መፍትሔ ለሆነው የዲሞክራሲያዊ ስርዓትና የህግ የበላይነት መስፈን በጽናት ሊቆም ይገባዋል።የተከፋፈለ ቤት አይጸናምና ወጣቱም በአንድነት በመቆም የዓላማ ጽናቱን ማረጋገጥ ይገባዋል። በተጨማሪም ወጣቱ ቅንጅት ፓርቲው ኢትዮጵያም ሀገሩ በመሆንዋ በከፍተኛ ተቆርቋሪነትና ተነሳሽነት በድርጅቱ ውሳኔ አሰጣጥ፤ አመራር፤ እንዲሁም ስራ አፈጻጸም መስክ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚችል በተግባር ያረጋገጠ በመሆኑ ይህንን አኩሪ ተግባር ለመቀጠል በጽናት መነሳት ይኖርበታል። የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግም ወጣቶች በቅንጅት ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ እንደሚያደረግና ለዚህም የፓርቲው ከፍተኛ አመራርና የድጋፍ ድርጅቶች ከፍተኛ ድጋፍና ይሁንታ እንዳለው ለማስታወስ ይወዳል።

የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ

ህዳር 27 2000 (December 4 2007)

ዋሽንግተን ዲ.ሲ.